# በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ሴክተር

# የ2013 በጀት ዓመት መነሻ እቅድ

ሐምሌ 2012 ዓ/ም

ሀዋሳ

ማውጫ ገጽ


1.መግቢያ---------------- --------------------------------------------------------------------------------1

2. የሴክተሩተልዕኮ፣ራዕይና እሴቶች------------------------------------------------------------------1

3. የሴክተሩ አጠቃላይ ገጽታ--------------------------------------------------------------------------3

4.የዕቅዱ ዓላማ ----------------------------------------------------------------------------------------4

5.የ የዕቅዱ ወሰን------------------------------------------------------------------------------------5

6.የአዘገጃጀት ዘዴ------------------------------------------------------------------------------------5

7. የእይታዎች መግለጫ-------------------------------------------------------------------------------5

8. የተገልጋይ እይታ ---------------------------------------------------------------------------------5

9. የፋይናንስ ዕይታ ----------------------------------------------------------------------------------6

10. የውስጥ አሰራር ዕይታ---------------------------------------------------------------------------6

11.የመማርና ዕድገት ዕይታ---------------------------------------------------------------------------7

12. የ2012 በጀት ዓመት ነባራዊ ሁኔታ ግምገማ-------------------------------------------------7

13.የትራንስፖርት ዘርፍ አፈፃፀም ግምገማ----------------------------------------------------------7

14. የመንገድ ልማት ዘርፍ አፈፃፀም---------------------------------------------------------------9

15. የ2013 በጀት ዓመት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፣ግቦች፣ውጤቶችና ዋና ዋና

ተግባራት በእይታ---------------------------------------------------------------------------------10

16. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች/Strategic Themes/------------------------------------------10

17. የሴክተር አቀፍ ግቦች/corporate Goals/ ---------------------------------------------------11

18.የሴክተር አቀፍ ውጤቶች /corporate Results/ ----------------------------------------------12

19.በአራቱ ዕይታዎች የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት-----------------------------------------------12

## 1.መግቢያ

ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ሴክተር በፌደራሉ ትራንስፖርት የመሠረትዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት አድርጎ ወደ ሙሉ ትግበራ በመሸጋገር የተጀመረውን የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተሟላ ለማድረግ አስፈላጊ ከሆኑት የለውጥ ስራዎች መካከል የውጤት ተኮር ሥርዓት በመሆኑ በዚህ ማሳኪያ ይሆን ዘንድ ባለንስድ ስኮርካርድ በሴክተር ደረጃ ተዘጋጅቶና ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በሴክተር ደረጃ የተዘጋጀውን የውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅትና ምዘና ስርዓት በዳይሬክቶሬትና በግለሰብ ፈፃሚ ደረጃ በማውረድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ከዚህ አንጻር በሴክተራችን ደረጃ የተዘጋጀውን ውጤት ተኮር ስትራቴጂ ዕቅድ መሠረት ባደረገ መልኩ በሴክተሩ የተጣሉትን ግቦች ያካተተ ውጤት ተኮር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 2.የሴክተሩ ተልዕኮ፣ራዕይና እሴቶች

### ተልዕኮ /Mission/

ለክልሉ ህብረተሰብ የተቀናጀ ልማት ለማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው መንገዶችን በማስጠናት፣በመገንባትና በማስገንባት እንዲሁም በመጠገንና በማስተዳደር፣የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በማስፋፋትና በማጠናከር፣የአሽከርካሪዎችንና የተሽከርካሪዎችን ብቃት በማረጋገጥ እና የህብረተሰቡን የመንገድ አጠቃቀምና ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ በማሳደግ የትራንስፖርት ተጠቃሚነትንና ደህንነትን እውን ማድረግና መላውን ህዝብ በማደራጀትና በማነቃነቅ በሴክተሩ ዕቅዶች ዝግጅት፣ አፈፃፀምና ውጤት ላይ ማሳተፍ መቻል፡፡

### ራዕይ /Vision/

በ2013 የክልሉ ህብረተሰብ ወደ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና አስተዳደራዊ ማዕከላትና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚያደርስ በቂ፣ምቹና አስተማማኝ የመንገድ አውታርና የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ ሆኖ ማየት፡፡

### እሴቶች

- ጥራት፣ግልጽነት፣ተጠያቂነትና ፍትሃዊነትን የሴክተራችን ሀብቶች እናደርጋቸዋለን፡፡
- ቀልጣፋ አገልግሎትና ውጤታማነትን ማረጋገጥ የተግባራችን ስኬት ዋና መለኪያዎች ናቸው፡፡
- ህብረተሰቡን ያሳተፈ ልማት ላይ እናተኩራለን፣
- ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ እንጠቀማለን፣
- በጋራ እንሠራለን ስኬቱም ውድቀቱም የጋራችን ነው
- የሙያ ስነ-ምግባር መጠበቅ መለያችን ነው፡፡
- ሙስናን እንፀየፋለን

- ለደንበኞቻችን እርካታ ቅድሚያ እንሰጣለን፡፡
- ውጤት ይሸለማል

**የሴክተሩ አጠቃላይ ገጽታ**

ትራንስፖርት ሴክተር የተለያዩ የአደረጃጀትና የአወቃቀር ሂደቶችን ያለፈ ተቋም ሲሆን በተሻሻለው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት/ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር _________/2012 መሠረት ተጠሪነታቸው ለቢሮው የሆኑ URRAP፤አሽ/ተሽ/ብቃ/ማረ፣መንገድ ትራ/ደህንነት ብቃ/ማረ፣ ህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃ/ማረ፣ የጭነት ትራ/አገ/ብቃት/ማረ/ ዳይሬክቶሬቶችንና እንዲሁም የዕቅድና በጀ/ዝግ/ክት/ግም፤ግዢ ፋይናንስና ንብረት አስ/ር፣የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር፣ ዘርፌ ብዙ ምላሽና፣ ሥ/ፆታን በልማት ማካተትና ተጠቃ/ማረጋገጥ፣ ስነ-ምግባር መከታታያ፣የሰው ሀብት መረጃ ስታትስቲክስና መረጃ ትንተናና ስርጭት የወል ዳይሬክቶሬቶችን በአደረጃጀት ያቀፈ ነው፡፡

በሴክተሩ ያለው ፓብልክ ሰርቫንት የመንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በጥልቀት አውቆና አምኖ የሴክተሩን የልማት ዕቅዶች ተፈጻሚ ለማድረግ እንዲችል የፓብልክ ሰርቫንት ማሻሻያ ሥራዎች በግንባር ቀደምትነት ተግባራዊ ሲደረጉ ከመቆየታቸውም በላይ የተገልጋዩን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሠረታዊ የአሠራር ስርዓት ለውጥ /BPR/ ጥናት ተካሂዶ፣አፈፃፀሙ በሙከራ ትግበራ ተገምግሞ ወደ ሙሉ ትግበራ ለመሸጋገር ተችሏል፡፡በሴክተሩ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሳለጥና ፈፃሚ አካል የሚመሩባቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች አዋጆች፣ደንቦች የአፈፃፀም መመሪያዎች እና የትግበራ ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በየደረጃው በሚመለከታቸው አካላት ጸድቀው ወደ ተግባር ተግብቷል፡፡ በመሆኑም ቀድሞ የነበረውን የሠራተኞች ምዘና ሥርዓት ትኩረቱ በውጤት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ለዜጐችና፣ለተገልጋዩ ፋይዳና እሴት በማይጨምሩ ልማዳዊ ተግባራት ዙሪያና በሠራተኞች ባሕሪይ ላይ ነበር፡፡ከዚህም በተጨማሪ የአረዳድ ሥርዓቶችንም በተጨባጭና በመርህ ላይ የተመሠረተ አልነበረም፡፡ስለሆነም የተጀመረውን የለውጥ ሂደት ቀጣይነት ለማረጋገጥ የኢንፎርሜሽን ዘመን በወለደው የሥራ አመራርና ውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ ባላንስድ ስኮርካርድ ሥርዓት ትግበራ በሴክተር ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

**የዕቅዱ ዓላማ**

የዚህ ዕቅድ ዓላማ ሴክተሩ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በስትራቴጂያዊ አስተሳሰብ ለመምራት ፣በሁሉም ደረጃ ባሉ ፈጻሚዎች መካከል ተግባቦትን ፈጥሮ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ እና ውጤቱንም መከታተል፣መለካትና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንዲያስችለው ለማድረግ ነው::

**የዕቅዱ ወሰን**

ይህ ዕቅድ የተዘጋጀው በትራንስፖርትና መንገድ ልማት ሴክተር ደረጃ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ ባለስልጣንና ቡድኖች ከዚህ ዕቅድ የድርሻቸውን ወስደው የሚተገብሩት ሲሆን ዕቅዱ የ2013-2022 የ10 ዓመት ሀገራዊ የትራ/መን/ል/ ዕቅድ ታሣቢ ያደረገው የ2013 ዓ.ም ዕቅድ ነው፡፡

**የአዘገጃጀት ዘዴ**

ይህ የውጤት ተኮር ዕቅድ በዋናነት መሰረት ያደረገው የአምስት ዓመቱን ስትሬቴጂክ ዕቅድ የ2017 ግብ መነሻ ያደረገ ሆኖ በ2012 ዓ.ም የተከለሰውን የሁለት ተከታታይ ዓመታት የጂቲፒ አፈጻጸም ላይ ቢሆንም በአዲስ መልክ የሚዘጋጀው በዓላማ ፈፃሚዎች ዳይሬክቶሬቶች ደረጃ የተጠናውን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፣ትራንስፖርት ሴክተር የተዘጋጀውን የBPR እና የተሻሻለውን የBSC ሰነዶች፣የልማት ኘሮግራሞች እና ሌሎች ሴክቶሪያል ሰነዶች እንደመነሻ በመውሰድ የተዘጋጀ ነው፡፡የዝግጅት ሂደቱና የዕቅዱ ይዘት በውጤት ተኮር ዕቅድ ግንባታና ትግበራ መሠረታዊ መርሆዎች የተቀመጡትን አቅጣጫዎች የተከተለ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡

**የተመረጡ እይታዎች ዝርዝር**

- ተገልጋይ
- ፋይናንስ
- የውስጥ አሰራር
- መማርና ዕድገት

**የእይታዎች መግለጫ**

**የተገልጋይ እይታ**

የተገልጋይ ዕይታ ማለት በሴክተሩ በሚሰጠው አገልግሎት ተገልጋዩ በአገልግሎት አሰጣጡ ምን ያህል እንደረካ በተገልጋዩ ዓይን ምን ዓይነት ገጽታ እንዳለው ራሱን የሚያይበት መነጽር /ዕይታ/ ነው፡፡

### የፋይናንስ ዕይታ

ፋይናንስ የደጋፊ ሥራ ሂደቱ ክንዋኔዎች መተግበሪያና የዕቅድ ማስፈፀሚያና መቆጣጠሪያ መሣሪያ በመሆኑ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ውጤታማ የሆነ አሠራር በማስፈን ውስን የሆነውን ሀብት በአግባቡ በመደልደልና ጥቅም ላይ መዋሉን ማየት የሚችልበት ዕይታ ነው፡፡ በመሆኑም ፋይናንስ እንደ አንድ እይታ የተወሰደው፡-

- የበጀት መረጃ በብቃትና በጥራት የተዘጋጀና ለሚመለከታቸው በወቅቱ እየተላለፈ ስለመሆኑ፣
- ለየሥራ ክፍሉ የተመደበው በጀት የተጣሉትን ግቦች በማስፈፀምና በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋሉ ስለመሆናቸው፣
- ከሴክተሩ የልማት አጋሮች በብድር በእርዳታና በድጎማ መልክ የሚመደብ ተጨማሪ ፋይናንስ ስለመገኘቱ

### የውስጥ አሰራር ዕይታ

ይህ የዕይታ መስክ የተመረጠበት ምክንያት በሴክተሩ በተገልጋይና እና ፋይናንስ ዕይታዎች አንፃር የነደፋቸውን ግቦች እንዴት ባለ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ለማሳካት አገልግሎቱን ለሚሰጠው የሴክተሩ ተቋማት ምን ተጨማሪ እሴት እንዳስገኘ ለማየት ስለሚያስችል ነው፡፡

- በምንሰጠው አገልግሎት ምን ያህል ተገልጋዮች እንደረኩና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት እንደቻልን ስለሚያሳይ
- ለተገልጋዩ ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሰጠንና ምን ተጨማሪ እሴት እንደጨመርን የሚያሳይ በሆኑ ነው፡፡

### የመማርና ዕድገት ዕይታ

የመማርና ዕድገት እይታ ማለት ተቋማት እና የሰው ሃይል በለውጥ ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሆኖ ለመኖር የሚያስችለውን ክህሎት፣ ችሎታ፣ የአሰራር ስርዓትና የሀብት አስተዳደር እና ከላይ የተጠቀሱትን የህዝብ፣ ይፋይናንስና የውስጥ አሰራር ዕይታዎችን ወደ ውጤት ለመለወጥ የሚያስችሉ አዕምሯዊና ረቂቅ የሆነ ድርጅታዊ ሃብቶች የሚካተቱበት እይታ ነው፡፡

- ካለን ሁሉ ሀብት ውድ የሆነውን የሰው ሀይል ለልማትና ለአፈፃፀም አጋዥ የሆኑ የስራ መሳሪያዎችን ምን ያህል እና እንዴት እየተጠቀምንበት መሆኑን
- የመረጃ አቅርቦት ቀልጣፋና አስተማማኝ መሆኑን
- ምቹ አደረጃጀት እና ጤናማ የስራ አካባቢ መፈጠሩን የሚያሳይ ዕይታ በሆኑ ነው፡፡

# ክፍል አንድ

## 2.የ2012 በጀት ዓመት ነባራዊ ሁኔታ ግምገማ

*የ2012 በጀት ዓመት የሴክተሩ የመሪ ዕቅድ አፈፃፀም በስትራቴጂክ ዕቅድ ከተቀመጡ ግቦች አንፃር ሲታይ ጥሩ ነው የሚባል አፈፃፀም ያለው ሲሆን በሂደቱ የነበሩ ጥንካሬዎችና ውስንነቶችን በሁለት ዘርፍ ከፋፍሎ ማየቱ የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ለማሻሻል እና የተከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ነው።በመሆኑም የትራንስፖርት አገልግሎት እና መንገድ ልማት ረገድ የታዩ ጥንካሬዎችና ውስንነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል።*

*በዚህ ክፍል በክልላችን ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በለውጥ ስራዎች፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ብልሹ አሰራርና ኪራይ ሰብሳብነት ተግባር እና በኪራይ ሰብሳብነት አመለካከት ላይ የተደረጉ ትግሎችን፣ እንድሁም ባለድረሻ አካላትን ባሳተፈ አሰራር የህዝብ ክንፍ ዕቅድ አፈጻጸምን ይዳሰሳል። በተጨማሪም በBsc ዕቅድ መሠረት የታቀዱት ሥራዎች አፈጻጸማቸው ምን እንደሚመስል ተገልጸአል።*

- ✓ ***የለውጥ ስራ አፈጻጸምን በሚመለከት***
  - *የለውጥ አመራር ስራዎችን ማለትም የBSC እና የBPR ስራዎችን ወደ ወረዳ /ከተማ በማውረድ ፈጻሚው ተግባራትን እየመዘገቡ ከመስራት አንፃር በተፈጠረው ለውጥና ከአመለካከት ጋር ባሉ ችግር መነሻ በተገቢው መልኩ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ለመለየት ተችሎአል።*
  - *በቢሮ □ሪ□ የማኔጅመንት፤የኮማንድ ፖስት፤የለውጥ ቡድንና የ1ለ5 አደረጃጀቶች በተቀመጠው ቋ□ መሰረት ውይይቶች የመንጠባጠብ ሁኔታ ይታያል፤ አብዛኛው አደረጃጀት ከሪፖርትና ግብረ መልስ አንጻር የተወሰኑቱ ጉድለት እ ንዳለባቸው ተገምግሞአል፤*
  - *በቢሮ ከለውጥ ቡድኖች (ከዳይሮክተሬቶች፣ከከዚ ቲም እና ከደጋፍ ስራ ሂደቶች ጋር) በአመታዊ ግብ ዙሪያ በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቶአል፡ ፡*
  - *በቢሮ ደረጃ 7 የለውጥ ቡድኖች እና 9 የ1ለ5 ቁርኝቶች ያሉ ስሆን የቁርኝቶችና የለውጥ ቡድኖች ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑን በድጋፊና ክትትል ማወቅ ተችሏል።*

*የ2012 በጀት ዓመት የ12 ወር አፈጻጸምን በመገምገም የቀጣይ ስራዎች አቅጣጫን በማስቀመጥና በትራንስፖርት ዘርፍና በመንገድ ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን በመጥራት የንቅናቄ ሰነድ ተዘጋጅቶ በተለይ የመንገድ ትራፍክ አደጋን ለመቀነስ ሰፊ ጥረት ተደርጎአል ።*

# *በመልካም አስተዳዳር ዙሪያ የተሠሩ ሥራዎች*

- ➢ *የመረጃና ስታሲቲክስ ክፍል/መዝገብ ቤትን/ በዘመናዊ የአይሲት መረጃ መረብ የማዘመን ስራ የመጀመሪያ ዙር ስራን በተሳካ ሁኔታ በመስራት ኮሚፒዩተራዝድ ለማድረግ መቻሉ፤*
- ➢ *ህገ ወጥ ሞተር ሳይክልን ህጋዊ በማድረግ እያስከተሉ ያሉትን የመልካም አስተዳደር ችግርና በሰዎች ላይ እየደረሰ ያለውን የህይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ*

በመምጣቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በክልላችን 5493 ሞተር ሳይክሎችን በህጋዊ በጉሙሩክ ታርፍ መሰረት ድክላራሲዮን እንድያገኙ ማድረግ ተችሎአል።

- የህዝብ ማመላለሻ ማህበራት አደረጃጀታቸውንና አሰራራቸውን በመመሪያና በደንቡ መሰረት እንድሆን የተደረገ ስሆን ከመመሪያና ከደንብ ውጭ ለረዥም ጊዜ በቦርድ አመራሪነት ሲያገለግሉ የነበሩትን አመራሮች በመመሪያና በደንቡ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ተወስዶአል።
- ከተለያዩ ክልሎችና ዞኖች ለሚመጡ በርካታ ህገ-ወጥ ፎርጅድ መንጃ ፈቃዶችን ለማጣራት ለሚመለከተው አካል እንድደርስ ተድርገዋል ፡
- ፎርጅድ ሠሌዳ፤የብቃት ማረጋገጫ፤ ሊብሬና መዉጫዎች ይዘው ለመጡ ህገ-ወጥ ግለሰቦችን በመያዝ ወደ ህግ አካል እንድጠየቁና ግንዛቤ እንድጨብጡ ተደርጓል።
- በየቀኑ ባለማቋረጥ የኪራይ ሰብሳብነት አመለካከትና ተግባር ላይ ጠንካራ ትግል ማድረግ መቻል
- ህብረተሰቡ ከኪራይ ሰብሳብነት አመለካከትና ተግባር እንድጠነቀቅ በየቀኑ የግንዛቤ ትምህርት መሰጠት ተችሏል።
- ክሊራንስ ሳይወስዱ የሚሄዱትን ተከታትሎ ከማስተካከል ረገድ ከማህበራት ጋር የመቀናጀት ሥራዎች ተሰርቷል።

## ያጋጠሙ ችግሮች

- በመልካም አስተዳደርና በክራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ላይ የሚደረግ ትግል ከላፉት አመታት አንፃር ከፍተኛ መቀዛቀዝ መታየቱ፤
- የለውጥ ስራዊትን ለመገንባት በተደረገው ጥረት በአደረጃጀትና አሰራር መመርያ መሰረት ከመስራት አንጻር ጉድለት እንዳለው ተገምግሞአል ፡፡
- በፈጻሚውና በአስፈጻሚው ዘንድ የለውጥ ስራዎችን እንደ ቁልፍ መሳሪያ አድርጎ የመውሰድ ጉድለት፤፤
- ከአንዳንድ ወረዳዎች የኮማንድ ፖስት ሪፖርቶችን ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ማግኘት ያለመቻልና የኮማንድ ፖስት ሪፖርትን በቼክ ሊስት መሠረት ያለማቅረብ፤
- በተወሰኑ ወረዳዎች የመናኃሪያ አለመኖር።
- የአሽከርካሪና ተሸካርካሪ ማዋቅር አንድ የሥራ ሂደት ላይ መሆኑ፤
- የአሽ/ማሰ/ተቋማት የሥልጠና አሠጣጥ ሂደት በቋሚነት ክትትል ያለማድረግ
- በመስክ የመሰናክልና የከተማ አነዳድ የፌተና ቦታ ምቹ ያለመሆኑ ችግር
- በኮምፕዩተር ፈተና በተለያየ ምድብ ውስጥ የተዘጋጁ የምዘና ጥያቀዎች ስህተት ያለባቸው መኖሩ።
- የመስክ ስራዎችን በወረዳ ለመደገፍና ክትትል ለማድረግ የተሽከርካሪ እጥረት ማጋጠሙ።
- በመንገድ ልማት ዘርፍ የመንገድ ግባአት(ሰሌክት ማቴሪያል እጥረት) እና ያለውንም በአግባቡ ለመጠቀም የአንዳንድ ወረዳ አመራሮች የአመለካከት ችግር ማነፃባረቃቸው፣
- የክልሉ መንገዶች ባለስልጣን ለመንገድ ስራ የሚበጀተውን በጀት በአግባቡ ጊዜውን በጠበቀ መልኩ ከማውረድ ይልቅ የበጀት ዓመቱ አጋማሽ በኃላ ማውረድ፣
- አልፎ አልፎ የምሰሩ መንገድ ፕሮጀክቶች የጥራት ጉድለት ያሉባቸው መሆን፣

- የመንገድ ስራ አማካሪዎች ስራዎችን በሰአቱ አጠነቀው ከማስረከብና አስፈላጊውን ለመንገዱ የምያስፈልጉ የተለያዩ ስትራክቸሮችን ያለማካተት፣
- በድስትርክቶች የሚሰሩ የመንገድ ፕሮጀክቶች መረጃቸው እንደየፕሮጀክታቸውና እንደየአከባቢያቸው ተለይተው በክልሉ መንገዶች ባለስልጣን ስላመይገለፁ ግልጽና ተጠያቅነት በሰፈነበት መልኩ ማስተዳደር ያለመቻል፣
- የድስትርክቶች አደረጃጀት የተንጠለጠለና ባለበትነትን የነፈገ መሆን፣ከዚህም መነሻ የድስትርክት አመራሮች ያላቸው የአመለካከት ችግር በስፋት መንፀባረቅ፣
- ድስትርክቶች ከቢሮው ጋር ተቀናጅተው ከመስራት አንፃር ክፍተት መኖሩ፣
- የመንገድ ትራፍክ አደጋን ለመቀነስ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም የ2012 በጀት አመት አፈፃፀም ካለፉት ሁለት ዓመታት አንፃር ስታይ የመረጃ ፍሰት ዝቅተኛ አፈፃፀም ያለ ብሆንም የአደጋው መጠን የመቀነስ ምልክቶችን እያሳየ መሆኑ።
- ከታችኛዉ መዋቅር መረጃዎች በወቅቱ አለመድረስ።
- ከመርሀ ግብር ዉጭ ለሆኑ ተሽከርካርዎች የስምርት መዉጫ ፈቃድ በመስጠት ማሰማራት።
- የማህበራት የቢሮ አደረጃጀት ዉስን መሆኑ
- ማህበራት የአባሎቻቸዉን መረጃዉን በትክክል መዝግበዉ አለመያዝ እና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት አለመቻል።
- አንድ አንድ ማህበራት ወርሃዊ የጉዞ ምልልስ ስታስትክ መረጃ ወሩን ጠብቀዉ አለማቅረብ።
- ከተቀመጠዉ አሰራር ሥራዓት ዉጭ የሆነ ህገ ወጥ የከተማ ትራንስፖርት አገለግሎት መበራከት።
- የደረቅ ጭነት መዋቅር ወደ ታችኛው አስተዳደር እርከን ያለመዉረድ
- የደረቅ ጭነት መናኃሪያዎች በክልልም ሆና በወረዳ ደረጃ ያለመኖራቸው

## የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የ1ለ5 እና የለውጥ ቡድን ውይይት ሪፖርትና ግብረ መልስ መቆራረጥን ለማስወገድ ከሁሉም አደረጃጀቶች ጋር ውይይት ተደርጎአል። በተጨማርም በአድስ መልኩ አደረጃጀቶችን የመከለስ ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- ከወረዳዎችና ከቀበሌዎች ስፋት አንጻር እንዲሁም የፕሮጀክቶች ስፋት አንጻር ስታይ ለክትትል ስራ የተሽከርካሪ የብቃት ጉድለት በማጋጠሙ በጀትን በማፈላለግ ወቅታዊ ጥገና ተደርጎ ለመፍታት ጥረት ተደርጎል ፤
- የቢሮው ማነጅመንት ፤ወረዳና ባለድርሻ አካላት በማቀናጀት ችግሮችን በተወሰነ ደረጃ ለመቅረፍ ጥረት ተደርጎአል ።
- በትራንስፖርት ዘርፍ ለሚፈጠሩ ችግሮች በተለየ መልኩ ድጋፊ ማድረግና የመፍትሄ እርምጃ የመውሰድ ስራዎች ተሰርተዋል።
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ተሰቷል።

- *ማህበራትን የማብቃትና የማጠናከር ሥራዎች ተሰርቷል።*
- *አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ለብቻው ሥራ ሂደት እንድሆን ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ መግለፅ*
- *የመስክ ፌተና ሜዳ ኮምፕለክስ እንድዘጋጅ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ሥራ ተሰርቶአል።*
- *ፎርጅድ መንጃ ፈቃዶችን ለመግታት ጠንካራ ግኑኝነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት መፍጠር*
- *ስህተት ያለባቸው የኮምፐተር ፌተና ጥያቄ ላይ እንድስተካከል ለክልል ትራንስፖርት ቢሮ የማሳወቅ ሥራ ተሰርቷል።*

## 2.1.የትራንስፖርት ዘርፍ አፈፃፀም ግምገማ

*በ2012 በጀት ዓመት ከተቀመጡ ስትራቴጂክ ግቦች አንፃር በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጥ ዘርፍ ከ5,078,000 በላይ ህዝብ በአግባቡ ማንጓዝ የተቻለቤት፣23 መናኸሪያዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ያገኙበት፣358 ተሽከርካሪዎች የደረጃ እድሳት የተደረገበት፣295 አዳዲስ ተሽከርካሪዎች የደረጃ ፍቃድ የተሰጠበት፣በመናኸሪያዎች አከባቢ የሚሰጠው የጫኚና አውራጆች አገልግሎት አሰጣጥ በመመሪያና ደንብ መሠረት ሆኖ ህዝቡን በአክብሮትና በተቀመጠው ታርፍ መሠረት እንዲያገለግሉ ማድረግ መቻል ዋና ዋና ጥንካሬዎች ናቸው።*

*ከአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ አንፃር አዲስ ብቃት ማረጋገጫ በማዘጋጀትና ፈትኖ በማረም 3,515 አሽከርካሪዎችን ማፍራት መቻሉ፣የተሽከርካሪዎችን ህጋዊነታቸውን፣ ብቃታቸውንና ልዩነታቸውን የሚያሳዩ ሰሌዳ 7,515፣ ሊብሬ 7,515፣ ቦሎ 7,515 እና የድሮ መንጃ ፈቃድ 4,050 በማሳተም ማሰራጨት መቻሉ፤ የአሽከርካሪ ብቃት ለማረጋገጥ 1 የአሽከአርካሪ ማሰልጠኛ ተቋመወ ለሚከፍቱ ብቃታቸውን በማረጋገጥ ፍቃድ የተሰጠበትና ዋና ዋናዎቹ ናቸው።*

*አንድ አዳዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበር ማደራጀት መቻል፤የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራን ለማሳለጥ በበጀት ዓመቱ አንድ አዲስ መናኸሪያ ግንባታ መጀመር የቦታ ዝግጅት የማጥናት ሥራ መሰራቱ ዋና ዋናዎች ናቸው።*

*ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት ብቃት ከማረጋገጥ አንፃር የትራፊክ አደጋ እያስከተለ ያለውን ጉዳት በመደበኛ ሥራ መወጣት ስላልተቻሌ በሀገር ደረጃ በንቅናቄና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግና ህዝቡን ማነቃነቅ በመቻሉና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍና ያለንን ውስን ሀብት ማስተባበር በመቻሉ የትራፊክ አደጋ እያስከተለ ባለው ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ዙሪያ 5,357,887 ለሚደርሱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር፤ በክልሉ ውስጥ 127 የተለያዩ ቦታዎች ላይ የእግረኛ ማቋረጫ ዜብራ ቅብ፤ ሲሆን፤የመንገድ ዳር ገላጭ ምልክት 53 የተተከለበት፤278 ጋሪዎች አንጸባራቂ እንዲለጥፉ*

*ማድረግ የተቻሌበት፣**365** ቀናት መደበኛ ቁጥጥር ሥራ ከትራፊክ ፖሊሶች ጋር በመቀናጀት ለመቆጣጠር የተቻሌበት፣የባለ ሁለት እግር ሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች ሄልሜት አለመጠቀማቸው በትራፊክ አደጋ ወቅት ለከፋ ጉዳት የሚዳርጋቸው መሆኑን በቂ ጊዜ ተወስዶና የተለያዩ ሚዲያዎችን ጭምር በመጠቀም በህብረተሰቡ ውስጥ ሰፊ የግንዛቤ ስራ የተሰራበትና በክልሉ ሀዋሳ ከተማን ጨምሮ ቁጥጥሩ ተግባራዊ የተደረገ ስሆን ምንም እንኳን የ2011 በጀት አመት የአደጋ መጠን ጭማሪ ብያሳይም ቁጥጥሩ ተግባራዊ በመደረጉ የተነሳ በአማካይ ለመጀመሪያ ጊዜ **ከ10 ዓመት ወድህ ንቀናቄው ከተጀመረበት መጋቢት 19/07/02-19/09/12 ድረስ ባሉት ጊዜያት ጠቅላላ አደጋ** ለመቀነስ ጥረት መደረጉ ዋና ዋና ጥንካሬዎች ናቸው፡፡*

**2.2 የመንገድ ልማት ዘርፍ አፈፃፀም**

*በበጀት ዓመት የመንገድ ልማት ዘርፍ ስራዎች አፈፃፀምን በተመለከተ በቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ ዘርፍ በ2004 እና 2005 ዓ.ም ተጀምረው ያልተጠናቀቁና የመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ የሆኑ ፕሮጀክቶችን በዚህ በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከባለድርሻ አካላት ጋር መረጃዎችን ማጥራትና ሥራዎች ተጠናቅቀው ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በመደረጉ፤ለሥራው ማነቆ የሆነውን የክፍያ፣ዲዛይንና ውሌታ መግባትና ማፅደቅን ሥራ ክልሉ በሰጠው ውክና መሰረት፤ከማህበራቶቹ ጋር ተደጋጋሚ ውይይትና ምክክር በማድረግ ተቋራጭ እና አማካሪ ማህበራት ከወትሮ በተለየ ሁኔታ የክልሉ መንግስት የሰጠውን ትኩረት ተረድቶ ወደ ሥራ እንዲሰማሩና በቁርጠኝነት እንዲሰሩ በመደረግና ተከታታይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ አቅማቸውን በማጎልበትና ማነቆዎችን በመፍታት በ2004 እና 2005 ዓ.ም ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ከተሸጋገሩ ነባር መንገድ ፕሮጀክቶች 23.35 ኪ.ሜ መካከል 7.5 ኪ.ሜ ጠጠር **የ**ማልበስ ሥራ መከናወኑ፣**ከቀር 80 ስትራክቸሮች** 17 የተለያዩ ስትራክቸሮችን መገንባትና፤ቀር 18ኪ.ሜ በ2012 ለማጠናቀቅ ዕቅድ የተያዘ ስሆን፤የድልድይ ግንባታ ሥራ በተመለከተ ከ10-20 ሜትር ርዝመት ያላቸው በ2008 ዓ.ም. ወል የተገባላቸዉ **የ10 ድልድዮች** ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ስሆን ቀር ስድስት ድልድዮች ግንባታቸው በመከናወን ላይ መሆኑ ዋና ዋና ጥንካሬዎች ናቸው፡፡*

# ክፍል ሁለት

## 3.3 የ2013 በጀት ዓመት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፤ግቦች፤ውጤቶችና ዋና ዋና ተግባራት በእይታዎች

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ሴክተር የ2011 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ አፈፃፀምን፤በክልሉ ምክር ቤት በፀደቀውና በBSC የተቃኘውን የ2ኛ ዙሪ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ /2008-2012/ መነሻ በማድረግ ዓመታዊ የሴክተሩን BSC ዕቅድ የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ግቦችንና ውጤቶችን ለማሳካት አቅዷል።

## 3.1 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች/Strategic Themes/

1.የትራንስፖርት አገልግሎት ማሳደግ

2.የመንገድ ልማት አገ/ት ማሳደግ

**የሴክተር አቀፍ ግቦች/corporate Goals/**

| ዕይታ | የግብ ተ.ቁ. | ሴክተር አቀፍ ግቦች/corporate goals/ |
|---|---|---|
| ተገልጋይ | 1 | የሴክተሩን ተገልጋይ እርካታና አመኔታ ማሳደግ |
| | 2 | የህብረተሰብ ተጠቃሚነትን ማሳደግ |
| ፋይናንስና በጀት | 3 | ሀብት አሰባሰብንና በጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ |
| የውስጥ አሰራር | 4 | የአሽከርካሪዎችን ዕውቀት፤ክህሎትና ሥነ-ምግባርን ማሻሻል |
| | 5 | የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃትን ማሳደግ |
| | 6 | የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል |
| | 7 | የመንገድ ትራፊክ አደጋን መቀነስ |
| | 8 | የመንገዶችንና ድልድዮችን ጥናትና ዲዛይን ጥራት ማሳደግ |
| | 9 | መንገዶችን በመገንባት ጥግግታቸውን ማሳደግ |
| | 10 | ድልድዮችን በመገንባት ቁጥራቸውንና ሽፋናቸውን ማሳደግ |
| | 11 | መንገዶችንና ድልድዮችን በመጠገን ማሻሻል |
| መማማርና ዕድገት | 12 | የፈፃሚውን አቅም ማሳደግ |
| | 13 | ውጤታማ የመረጃ አያያዝና የኮሙኒኬሽን ሥርዓት ማሳደግ |

**የሴክተር አቀፍ ውጤቶች /corporate Results/**

| ዕይታ | የግብ ተ.ቁ. | ሴክተር አቀፍ ውጤቶች /corporate Results/ |
|---|---|---|
| ተገልጋይ | 1 | ያደገ የተገልጋይ እርካታና አመኔታ |

| | | |
|---|---|---|
| | 2 | ያደገ የህብረተሰብ ተጠቃሚነት |
| ፋይናንስና በጀት | 3 | የተሻሻሌ የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም |
| የውስጥ አሰራር | 4 | የተሸሻለ የአሽከርካሪዎች ዕውቀት፤ክህሎትና ሥነ-ምግባር |
| | 5 | ብቃታቸው ያደገ ተሽከርካሪዎች |
| | 6 | የተሻሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ |
| | 7 | የቀነሰ የመንገድ ትራፊክ አደጋ |
| | 8 | ብቃት ያለውና ውጤታማ የሆነ የመንገዶችና ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን |
| | 9 | ተገንብቶ የተጠናቀቁ መንገዶች |
| | 10 | ተገንብቶ የተጠናቀቁ ድልድዮች |
| | 11 | ተጠግነው የተጠናቀቁ መንገዶችና ድልድዮች |
| መማማርና ዕድገት | 12 | ያደገ የፈፃሚዎች አቅም |
| | 13 | ተደራጅቶ የተያዘና የተሰራጨ መረጃ |

**4.በአራቱ ዕይታዎች የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

**4.1.ተገልጋይ ዕይታ**

**ግብ 1 የሴክተሩን ተገልጋይ እርካታና አመኔታ ማሳደግ**

**ውጤት፡-ያደገ የተገልጋይ እርካታና አመኔታ**

4.1.1 ተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድና አገልግሎትን ማሻሻል

1.1.2 ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ስለ አገልግሎት አሰጣጥ የተለያዩ ውይይቶችን ማካሄድ

4.1.3 በጥናቱ ግኝትና ውይይቶች መነሻ የማሻሻያ ስልቶችን መንደፍና ማቅረብ

**ግብ 2 የህብረተሰብ ተጠቃሚነትን ማሳደግ**

**ውጤት፡-በመንገድ ልማትና ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ህብረተሰብ**

4.2.1 በትራንስፖርት ዘርፍ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ቁጥርን መጨመር፣

4.2.2. በመንገድ ዘርፍ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ቁጥርን መጨመር፣

**4.2 ፋይናንስና በጀት**

**ግብ፡-3 ሀብት አሰባሰብንና በጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ**

**ውጤት፡-የተሸሻሌ የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም**

4.3.1. የበጀትና የፊዝካል ዕቅድ አፈጻጸምን ማጣጣም

4.3.2 በህብረተሰብ ተሳትፎ የቀበሌ ተደራሽ መንገዶችን ግንባታ 50% ለማሳካት ከህብረተሰቡ የሚሰበሰብ ገንዘብና ጉልበት የገንዘብ ምጣኔን ማሳደግ

### 4.3 ከውስጥ አሰራር አንፃር

**ግብ 4 የአሽከርካሪዎችን ዕውቀት፤ክህሎትና ሥነ-ምግባርን ማሻሻል**

**ውጤት፡-ዕውቀት፤ክህሎትና ሥነ-ምግባራቸው የተሻሻሉ አሽከርካሪዎች**

4.4.1 በቢሮ ደረጃ የሚዘጋጁ ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች ላምኔትድ ማድረግ

4.4.2 የቀድሞ መንጃ ፈቃዶችን ቅጂ ማሳተም፣

4.4.3 በቢሮ የሚዘጋጁ አዲሱን የካታጎሪ የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ማዘጋጀት፣

4.4.4 ነባርና አዳዲስ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን የመፈጸም አቅም ማጠናከር

4.4.6 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ለሚወስዱ እጩ አሽከርካሪዎች የሚሰጥ የምዘና ጥያቄዎችን ማዘጋጀት

**ግብ 5 የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ማሳደግ**

**ውጤት ፡-የቴክኒክ ብቃታቸው የተረጋገጡ ተሽከርካሪዎች**

4.5.1. ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ማድረግና ቦሎዎችን መግዛት

4.5.2 ሰሌዳዎችን ማሳተም፣

4.5.3 የተሽከርካሪ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ መግዛት

4.5.4 ለተሽከርካሪዎች የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ቅጻቅጾችን መግዛት፣

4.5.5 የተሽከርካሪ ምርመራ ማዕከላትን የመፈጸም አቅም ማጎልበት

4.5.7 የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ማዘጋጀት

4.5.8 በአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ለሚሰጡ አገልግሎቶች የክፍያ ታሪፍ በማዘጋጀት አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ፣

4.5.9. የአዳዲስ ተሽከርካሪዎችን መረጃ ማደራጀት

4.5.10 ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ቁጥጥር/ምርመራ ማድረግ

4.5.11 አዲስ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪዎችን መረጃ ማደራጀት፣

**ግብ 6 የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል**

**ውጤት፡-የተሻሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ**

**4.6.1** ክልሉን ከአጎራባች ክልሎች የሚያገናኘውን የሥምሪት መስመር ቁጥር ማሳደግ

4.6.2 በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ የከተማና የገጠር የስምሪት መስመሮችን ማሳደግ

4.6.3 በክልሉ አሁን ያሉትን የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ማሳደግ

4.6.4 በክልሉ የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ የሚሰጡ ማህበራትን ቁጥር ማሳደግ

4.6.5 የመለስተኛ እና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎችን በአክስዮን እንዲደራጁ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ

4.6.6 የመካከለኛ የህዝብ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያ ዲዛይንና ቴክኖሎጂ ማዘጋጀት፣

4.6.7.በከተሞች በተጠኑ የስምሪት መስመሮች ላይ የተሳፋሪ መጫኛና ማውረጃ ቦታዎችን መለየት፣

4.6.8.የ1ኛ ደረጃ መናኸሪያ የአከባቢና የግንባታ ፕላን እንዲዘጋጅ ማድረግ

4.6.9. የ2ኛ ደረጃ መናኸሪያ የአከባቢና የግንባታ ፕላን እንዲዘጋጅ ማድረግ

4.6.10 የ3ኛ ደረጃ መናኸሪያ የአከባቢና የግንባታ ፕላን እንዲዘጋጅ ማድረግ

4.6.11 መናኻሪያዎችን ደረጃ ማሻሻል

4.6.12 አዲስ መናኸሪያዎችን መገንባት፣

4.6.13 መናኽሪያዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ ማድረግ

4.6.14 መናኻሪያዎችን በዋይዳል ኤሪያ ኔት ወርክ ማገናኘትና የመረጃ አያያዝ፣ትንተናና ሥራጭት ዘዴውን ዘመናዊ ማድረግ

4.6.15 የህዝብ ትራንስፖርት ፌርማታዎችን ማልማትና ሸዶችን መገንባት

4.6.16 የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች መለየትና መከለል

4.6.17 የታክሲ ማህበራትን በከተሞች ማደራጀት

4.6.18 የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ

4.6.19 አዳዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን ማደራጀት

4.6.20 በጭነት ትራንስፖርት በድርጅት ወይም በኩባንያ ለሚደራጁ ባለሀብቶች የደረጃ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት

4.6.21 የጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ የግል ኦፕሬተሮች አደረጃጀት በጭነት አይነት /Specialization/ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ

4.6.22 በክልሉ የሚገኙ የጭነት ተሸከርካሪዎች መረጃ በመጫን ችሎታ፤በደረጃ እና በአገልግሎት ዘመን ማደራጀት (incod) ማድረግ

4.6.23 ለጭነት ተሸከርካሪዎች ማረፊያ/መናኸሪያ በተመረጡ የዞን ወረዳና ከተማ አስ/ር በመገንባት የመናኃሪያዎችን ቁጥር ማሳደግ

**ግብ 7 የመንገድ ትራፊክ አደጋን መቀነስ**

**ውጤት፡-የቀነሰ የመንገድ ትራፊክ አደጋ**

4.7.1በዞኑ/በክልሉ/ ለሚገኙ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት

4.7.2 ዓለም አቀፍ የመንገድ ዳር ምልክቶችን መትከል

4.7.3 የእግረኛ ማቋረጫ/ዜብራ/ መቀባት

4.7.4 የመንገድ ዳር ጽሁፍ/ ገላጫ/ምልክት ማኖር

4.7.5 በክልል ደረጃ በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠም የፍጥነት መቆጣጠሪያ ራዳር እንዲኖር ማድረግ

4.7.6 በወረዳ ደረጃ በእጅ የሚያዝ የፍጥነት መቆጣጠሪያ ራዳር እንዲኖር ማድረግ

4.7.7 በእንስሳት የሚሳቡ ጋሪዎች ላይ አንጸባራቂ ምልክት ማድረግ

4.7.8 ለአደጋ መንስኤ የሚሆኑ ቦታዎችን በጥናት በመለየት በግልፅ የሚታዩ ቢል ቦርዶችን መትከል

4.7.9 በክልሉ መንገዶች በከፍተኛ ፍጥነት ምክንያት ለአደጋ መንስዔ የሚሆኑ ቦታዎችን በጥናት በመለየት በካርታ ላይ ማስፈር

4.7.10 በትምህርት ቤቶች ውስጥ አዲስ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ክበባትን እንዲቋቋሙ ማድረግ፣

4.7.11 በመንገድ ዳር በሚገኙ ቀበሌዎች አዲስ የመንገድ ደህንነት ኮሚቴዎችን በማቋቋም ቁጥራቸውን ማሳደግ

4.7.12 አጠቃላይ የመንገድ ትራፊክ አደጋን መቀነስ

4.7.13 አጠቃላይ የንብረት ጉዳት /በገንዘብ /እንዲቀንስ ማድረግ

4.7.14 አጠቃላይ የህይወት ጉዳት /ሞት/እንዲቀንስ ማድረግ

4.7.15 የመንገድ ላይ ቁጥጥር ማድረግ

4.7.16 ሚድያዎችን በመጠቀም ህብረተሰቡን ማስተማር

**ግብ 8 የመንገዶችንና ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን በማዘጋጀት መጨመር**

**ውጤት፡-የተዘጋጀ የመንገዶችና ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን**

4.8.1 የነባርና አዲስ መንገዶች ጥናትና ዲዛይን ማከናወን

4.8.2.የነባርና አዲስ ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን ማከናወን

**ግብ 9 መንገዶችን በመገንባት ጥግግታቸውን ማሳደግ**

**ውጤት፡-ተገንብቶ ያደገ መንገዶች ጥግግት**

4.9.1 ከባለፈው በጀት ዓመት የተሸጋገሩ ነባር መንገዶችን በመገንባት የመንገድ ጥግግቱን ማሳደግ

4.9.2 አዳዲስ መንገዶችን ግንባታ በማከናወን የመንገድ ጥግግቱን ማሳደግ

4.9.3 ነባር የአፈር ሥራው አልቆ ጠጠር ያልበሱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ጠጠር በማልበስ ጥግግቱን ማሳደግ

4.9.4 ዲዛይናቸው የተጠናቀቁ የቀበሌ ተደራሽ መንገዶች 50% የአፈር ሥራ፣ምንጣሮና ጠረጋ በህብረተሰብ ተሳትፎ በመሥራት በቀጣይ ጠጠር ለማልበስ ዝግጁማሳደግ

4.9.5 በህዝብና በባለድርሻ አካላት ተነሳሽነት መንገዶችን በመገንባት የመንገድ ጥግግቱን ማሳደግ

**ግብ 10 ድልድዮችን በመገንባት ቁጥራቸውንና ሽፋናቸውን ማሳደግ**

**ውጤት፡-ተገንብቶ የተጠናቀቁ ድልድዮች**

4.10.1 ከባለፈው በጀት ዓመት የቀጠሉ ድልድዮችን ግንባታ ማከናወን

4.10.2 በበጀት ዓመቱ አዳዲስ የድልድይ ግንባታ ማከናወን

4.10.3 በዩራፕ መንገድ ላይ የተለያዩ ስትራክቸሮችን ግንባታ ማከናወን

**ግብ 11 መንገዶችንና ድልድዮችን በመጠገን ማሻሻል**

**ውጤት፡-ተጠግነው የተጠናቀቁ መንገዶችና ድልድዮች**

4.11.1 በክልሉ የሚገኙ መንገዶችን ወቅታዊ ጥገና ማድረግ

4.11.2 በክልሉ የሚገኙ መንገዶችን መደበኛ ጥገና ማድረግ

4.11.3 በክልሉ የሚገኙ መንገዶችን በርዝመት በሰው (Length Person) ጥገና ማድረግ

4.11.4 በቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ ፕሮግራም የመንገድ ጥገና ማካሄድ

**4.4 መማማርና ዕድገት ዕይታ**

**ግብ.12.የሴክተሩን አመራሮችና ባለሙያዎችን የመፈፀሚና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ**

**ውጤት፡-አቅማቸው የተገነቡ አመራሮችና ባለሙያዎች**

4.12.1.ለባለሙያዎችና አመራሮች አቅም ሊያሳድጉ የሚችሉ ሥልጠና መስጠት

4.12.2.የልምድ ልውውጥ ማድረግ፤

4.12.3 አከባቢውን ለሥራ ምቹ ማድረግ፤

**ግብ 13 ውጤታማ የመረጃ አያያዝና የኮሙኒኬሽን ሥርዓት መዘርጋት**

**ውጤት፡-ተደራጅቶ የተያዘና የተሰራጨ መረጃ**

4.13.1 ከዞኖችና ከወረዳዎች የሚያገናኝ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ኔትወርክ ሲስተም ለመዘርጋት ከክልል ጋር መቀናጀት፤

4.13.2 በክልሉ የመንገድ ነትወርክ ማደራጀት

# በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ሴክተር የቀበሌ ተደራሽ መ/ግ/ ዘርፍ የ2013 ዓ/ም ዓመታዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ

| ተቁ | ዕይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት % | መለኪያዎች | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች - | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብዓመት | | | | ፈጻሚ አካል | በጀት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | | | |
| 1 | የውስጥ አሰራር 60% | በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት በURRAP ፕሮግራምተጀምሮ ያልተጠናቀቁ መንገዶችን ማጠናቀቅ በ2006 በጀት ዓመት በURRAP ፕሮግራምየታቀዱ መንገዶችን የቅየሳና የዲዛይን ስራ ማስራት | 8% | የተገነባና ለአገልግሎት የበቃ የጠጠር መንገድ በኪ.ሜ | 2% | 18 | 372 | | | | | | | |
| | | | | የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በኪ.ሜ | 1% | | 508 | | | | | | | |
| | | | | የተገነባ የአፈር መንገድ በኪ.ሜ | 2% | | 300 | | | | | | | |
| | | | | በዓመቱ የተያዘ የፕሮጀክት ቁጥር /ኪ.ሜ/ | 1% | | 1580 | | | | | | | |
| | | | | የቅየሳና የዲዛይን ስራን በመከታተል ጥራትን በማስጠበቅ BOQ ማጸደቅ በፕሮጀክት ቁጥር | 2% | 390 | 258 | | | | | | | |
| | | በ2006 በጀት ዓመት በURRAP ፕሮግራም የታቀዱ መንገዶችን የቅየሳና የዲዛይን ስራ | 4% | በURRAP ፕሮግራምየተሰራየመንገድጥገና በኪ.ሜ | 4% | 265 | | | | | | | | |
| | | ለሚገነቡ መንገዶች በየደረጃቸው የስትራክቸር ስራዎችን ለይቶ ማሰራት | 3% | ለሚገነቡ መንገዶች በየደረጃቸው የስትራክቸር ስራዎችን ለይቶ ማሰራት | 3% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | የመንገድ ግንባታ መረጃዎችን በሀርድ በሶፍት ኮፒ ማደራጀትና ማሰራጨት | 3% | የመንገድ ግንባታ መረጃዎችን በሀርድ በሶፍት ኮፒ ማደራጀትና ማሰራጨት | 3% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | ለተቋራጮች በሊዝ የተሰራጨ አነስተኛ ማሽነሪዎች ዋጋ ተመላሽ ልያደርግ የሚገባውን የገንዘብ መጠን በክፍያ ሰርተፍኬቱ ውስጥ ተካቶ እንድቀርብ ማድረግና መረጃውን ማደራጀት | 6% | እንደማጣ | 6% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | በዞኑ የተመደቡ ከባድ የኪራይ ማሽነሪዎች ተከራይተው መስራት ለሚፈልጉ ማህበራች በመመሪያው መሠረት ማስፈፀም | 15% | የኪራይውል ማዘጋጀትና ለማሟያ ማቅረብ እንደማጣ | 3% | | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | | የማሽነሪ አጠቃቀም ክትትል ተደርጎ ለመምሪያ የቀረበ ሪፖርት በዙር | 3% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | የተደራጀ የቀበሌያት መረጃ በዙር | 3% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | የወረዳና የዞኑን የመንገድ ኔት ወርክ ማዘጋጀት በዙር | 3% | 2 | 2 | 1 | | | 1 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወረዳዎች ለሚገነቡት ለድልድይ ግንባታ ሙያዊ ድጋፊ ማድረግ በዙር | 3% | 6 | 12 | 4 | 4 | 4 | 4 | | | |
| | | በጉልበትና አነስተኛ እውቀት በሚሰሩ ስራዎች ለ10,000 ሰራተኞች ለ8,000 ወንዶችና ለ2,000 ሴት ወጣቶች በተደራጀ መልኩ በማሳተፍ የስራ ዕድል መፍጠር | 6% | በጉልበትና አነስተኛ እውቀት በሚሰሩ ስራዎች ለ10,000 ሰራተኞች ለ8,000 ወንዶችና ለ2,000 ሴት ወጣቶች በተደራጀ መልኩ በማሳተፍ የስራ ዕድል መፍጠር | 6% | 10,000 | | 2000 | 3000 | 3000 | 2000 | | | |
| | | በመንገድ ግንባታ ስራ ላይ ጠረጋ ምንጣሮና የ50% የአፈር ስራ በህብረተሰብ ተሳትፎ ማረጋገጥ | 3% | በመንገድ ግንባታ ስራ ላይ ጠረጋ ምንጣሮና የ50% የአፈር ስራ በህብረተሰብ ተሳትፎ በማረጋገጥ 200,000 ማድረስ በሰው | 3% | | 300 | | 100 | 100 | 100 | | | |
| | | ከመንገድ ግንባታ ጎን ለጎን የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በህብረተሰብና በባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት | 3% | ከመንገድ ግንባታ ጎን ለጎን የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በህብረተሰብና በባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ኪ.ሜ | 3% | 1274 | 1580 | | 526.6 | 526.6 | 526.6 | | | |
| | | በዞኑ አቅም በከተማ/ ወረዳዎች የመንገድ ጥገናና የድልድይ ግናባታ ስራዎችን ማከናወንና ወረዳዎች ለሚገነቡት ድጋፍ መስጠት | 9% | በዞኑ ግሬደርና ሎደር የተጠገነ መንገድ በኪ.ሜ | 3% | 100 | 174.65 | | | | | | | |
| | | | | በዞኑ በጀት ለወረዳዎች ዘጠኝ አዳዲስ ድልድዮችን ማስገንባት | 6% | 3 | 9 | | 3 | 3 | 3 | | | |
| 2 | በጀት10 % | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | 10% | በበጀት ዓመቱ ለመደበኛና ለካፒታል የተመደበ በጀት ከተሰሩ ስራዎች ጋር ያለው ንጽጽር % | 10% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| 3 | ተገልጋይ 20% | የፊዚካልና ፋይናንሻል ስራ ተመጣጣኝ መሆኑን እተረጋገጠ የሚቀርቡ የክፊያ ሰርትፍኬትና ሪፖቶች | 10% | የተገነቡ መንገዶችን ጥራት መከታተል መገምገምና በጽሁፍ የተዘጋጀ ሪፖርት ማቅረብ በዙር | 10% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | 4% | የክፍያ የገንዘብ መጠን ከፊዚካል ስራው ጋር የተጣጣመ መሆኑ ተረጋግጦ የቀረበ የክፍያ ሰርተፍኬት እንደመጣ | 4% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | 4% | የየሩብ ዓመቱ የተዘጋጀ ሪፖርት | 4% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | 2% | በየ15 ቀኑ የቀረበ የለውጥ ቡድን የውይይት ሪፖርት በዙር | 2% | 24 | 24 | 6 | 6 | 6 | 6 | | | |
| 4 | መማሪና ዕድገት 10% | የተለያዩ አመራሮች ባለሙያዎችና ፈጻሚዎችን አቅም በተለያየ ስልጠናዎች መገንባት በቁጥር | 7% | 5 ጊዜ የመምሪያ ኃላፊን ጨምሮ የስራ ሂደቱ ባለሙያዎች ከክልል መንገዶች ባለሥልጣንና ከአቻ ዞኖች የልምድ ልዉዉጥ እንዲቀስሙ ማድረግ | 4% | | 2 | | 1 | | 1 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ለ115 በወረዳዎች ለተሰማሩ ባለሙያዎች በቀበሌ ተደራሽ መንገድ ግንባታ የሥራ ሂደት በመንገድ ግንባታና ጥገና፣ የፕሮጀክት አስተዳደር፣ ግምገማ ዝግጅት፣ የመረጃ አያያዝና ሪፖርት አዘገጃጀት ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት በ10 ዙር መስጠት | 3% | | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | ለዞኑ URRAP ባለሙያዎች ፣ ለስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት | 3% | በተሰጠው ስልጠና ግንዛቤ የጨበጡ ፈጻሚዎች፣ የስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች በቁጥር | 3% | 200 | 250 | 50 | 50 | 100 | 50 | | | |
| | | | | | | | | | | | | | 800,000 | |

# አሽ/ተሽ/ ብቃት ማረ/ ቡድን የ2013 ዓ.ም ዓመታዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ

| ተቁ | ዕይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት % | መለኪያዎች | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች - | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | | ፈጻሚ አካል | በጀት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | | | |
| 1 | ተገልጋይ 20% | የአሽ/ብቃ/ማረጋገጫ ልዩ ልዩ የመንጃፈቃድ አገልግሎት መስጠት | 4% | አዲስ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ዕጩ አሽከርካሪዎች በቁጥር | 2% | 7000 | 6000 | 1500 | 1500 | 1500 | 1500 | | | |
| | | | | የታደሱ መንጃ ፍቃዶች በቁጥር | 1% | | 1000 | 250 | 250 | 250 | 250 | | | |
| | | | | የተለወጡ ቅጂ የተሰራላቸው መ/ፍቃዶች በቁጥር | 1% | 7000 | 5060 | | | | | | | |
| | | 1200 ነባር መ/ፍቃዶችን ወደ አዲስ ብቃት ማረጋገጫ መለወጥ | 3% | ወደ አድስ የተለወጡ መንጃ ፍቃዶች | 2% | 5000 | 7000 | 200 | 200 | 150 | 150 | | | |
| | | ከዞን ወደ ዞን የፋይል ዝውውር ማድረግ | 2% | ዝውውር የተደረገላቸው ፋይሎች | 2% | | 6000 | | | | 7 | | | |
| | | ለ500 ተቀጣር ሾፈሮች ብቃታ ማረጋገጥ | 1% | ለ ተቀጣሪ ሾፌሮች ብቃት ማረጋገጥ | 1% | 280 | 280 | 90 | 90 | 100 | 100 | | | |
| | | 8 በፍርድ ቤት ስማቸውን ለሚቀይሩ አገልግሎት መስጠት | 1% | በፍርድ ቤት ስማቸውን የቀየሩ | 1% | 8 | | | | | | | | |
| | | አድስ ተሽከርካሪ ምዝገባ ማድረግ ሰሌዳ መስጠት፤የድንገተኛ ምርመራ ተደርጎ ተለጣፊ ቦሎና የጠፋ ሊብሬ ቦሎና ሰሌዳ መስጠት | 9% | ምዝ/ተደርጎ ሰሌዳና ሊብሬ የተሰጣቸው አዳዲስ ተሽከርካሪዎች | 2% | 3950 | 3500 | | | | | | | |
| | | | | ተሽከርካሪ የቀለም ለውጥ አገልግሎት መስጠት | 1% | 3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | ለ ተሽ/ሞተር ለውጥ አገልግሎት | 1% | 2 | 2 | | | 1 | 1 | | | |
| | | | | ለተሽከርካሪ የአካል ለውጥ አገልግሎት መስጠት | 1% | 3 | 4 | | 1 | 1 | 2 | | | |
| | | | | የጠፋ ቦሎ ምትክ መስጠት | 1% | 10 | 8 | 2 | 2 | 2 | 2 | | | |
| | | | | ለጠፋ ሰሌዳ ምትክ መስጠት | 1% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | ድንገተኛ ምርመራ የተደረገላቸው ተሽከርካሪዎች | 1% | | 1200 | 300 | 300 | 300 | 300 | | | |
| | | | | የጠፋ ሊብሬ  የወሰዱ | 1% | | 14 | 3 | 3 | 4 | 4 | | | |
| | | | | አመታዊ ተሽ/ምር/ተለጣፊ ቦሎ የወሰዱ | 1% | 4232 | 4000 | 1000 | 1000 | 1000 | 1000 | | | |
| 2 | በጀት10 % | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | 10% | የተመደበው በጀትና የተሰሩ ስራዎች ንጽጽር | 10% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | የውስጥ አሰራር | ለ360 ተሽ/የዋጋ ግምት መ፣ከናወንና የስም ዝውውር | 5% | የዋጋ ግምት የተሰራላቸውና የሽያጭ ቀረጥ ከፍለው ስም የተዛወረላቸው | 5% | 358 | 360 | 90 | 90 | 90 | 90 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 60% | ማድረግ | | ተሽከርካሪዎች | | | | | | | | | | |
| 3 | | ለ360 ተሽ/ባለቤትነት ስም ዝውውር ማድረግ | 4% | የተሽ/ባለቤትነት ስም ዝውውር ማድረግ | 4% | 358 | 360 | 90 | 90 | 90 | 90 | | | |
| | | ከሌላ አከባቢ ለመጡና አካባቢውን ለሚለቁ ተሽከርካሪ ምዝገባ ማድረግ | 4% | ከሌላ ክልል መጥተው የተሽ/ምርመራ በማድረግ ሰሌዳ ያወጡ ተሽ/ዎች | 2% | 80 | 150 | 37 | 37 | 37 | 38 | | | |
| | | | | ከዞናችን ወደ ሌላ ክልል የሄዱ ተሽ/ዎች | 2% | 80 | 120 | 30 | 30 | 30 | 30 | | | |
| | | ለ80 ተሽከርካሪ እዳና እገዳ ማጣራትና ማገድ | 4% | እዳና እገዳ የተጣራና የታገደ 80 ተሽከርካሪ | 4% | 52 | 80 | 20 | 20 | 20 | 20 | | | |
| | | የጋራዥ እንስፔክሽን ማድረግ | 2% | እንስፔክሽን የተደረገላቸው ጋራዦች | 2% | -- | 2 | 1 | 1 | | | | | |
| | | ለጋራዥ የደረጃ ምደባ መስጠት | 2% | 5 የደረጃ ምደባ የተሰጠው ጋራዥ | 2% | -- | 1 | 1 | | | | | | |
| | | የአሽ/ተሽ መረጃ በኮምፒዩተር ማደራጀትና ማስተላለፍ | 7% | የተደራጀና የተላለፈ መረጃ በዙር | 7% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | 10000 በቀድሞ በየደረጃው የተሰጡ መንጃ ፈቃዶችን መዝግቦ መያዝ | 6% | 10000 ተመዝግቦ መረጃ የተያዘላቸው መንጃ ፈቃዶች | 4% | 10000 | 17,000,000 | 3500 | 3500 | 5000 | 5000 | | | |
| | | የማሰልጠኛ ተቋማቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 7% | በነባሮቹና በአድሶቹ ተቋማት ላይ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በምልልስ | 7% | 945 | 770 | 192 | 192 | 192 | 192 | | | |
| | | የተቋማት አለማማጅ ምዝገባና እድሳት ማድረግ | 6% | አለማማጅ ተሽከርካሪዎች ምዝገባና እድሳት የተደረገላቸው ተቋማት በቁጥር | 5% | 9 | 13 | 3 | 3 | 3 | 4 | | | |
| | | በተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ተቋም ስራ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶቸች የቅድመ ፈቃድ ድጋፍና ክትትል | 7% | በተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ተቋም ስራ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶቸች የቅድመ ፈቃድ ድጋፍና ክትትል | 3% | እንደመጣ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | የተለያዩ የአሽከርካርና የተሽከርካሪ ህትመቶችን ማሳተም | 5% | በአራት ዙር የቦሎ ፤የሊባሬና የታርጋ ህትመቶችን ማሳተም | 6% | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| 4 | መማማሪ ና ዕድገት 10% | ለነባር አሽርካሪዎች ፤ለባለሙያዎችና ለባለሀብቶች ስልጠና መስጠት | 10% | 200 የተሀድሶ ስልጠና የወሰዱ ነባር አሽከርካሪዎች | 1% | 50 | 200 | 50 | 50 | 50 | 50 | | | |
| | | | | የአፕሩቫለ ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች | 1% | -- | 1 | | | 1 | | | | |
| | | | | የማሰልጠኛ ተቋማት ለመክፈት ለሚፈልግ ባለሀብት የቀድመ ፈቃድ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | 2% | -- | እንደመጣ | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | | የአሽ/ተሽ አያያዝን በሚመለከት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ብሮሽሮችና ጽሁፎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት | 2% | 1 | 1 | | | 1 | | | | |
| | | | | በዜጎች ቻርተር ዕቅድ መሰረት ከተገልጋዮች ጋር የተደረገ የውይይት መድረክ | 1% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | ስልጠና የወሰዱ የጋራዥ ባለሀብቶች | 1% | እንደመጣ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | | ለአሽ/ማሰልጠኛ ተቋሚት ባለቤቶች፤ ለአሰልጣኞችና ለሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት በዙር | 2% | 2 | 2 | | 1 | | 1 | | | |

# የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ቡድን የ2013 ዓ/ም ዕቅድ

| ተቁ | ዕይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት % | መለኪያዎች | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች- | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብዓመት | | | | ፈጻሚ አካል | በጀት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | | | |
| | ተገልጋይ 20% | የማበረታቻ ሥራዎች | | በዞን ደረጃ በመንገድ አጠቃቀም ለውጥ ያመጡ እና የመንገድ ትራፊክ አደጋና የአደጋ ጉዳት የቀነሱ 3ወረዳ አወዳድሮ መሸለም | 6% | 3 | 3 | - | - | - | 3 | | | |
| | | | | በእግረኛ የመንገድ አጠቃቀም የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን ቀበሌዎች በወረዳና በከተማ አአስተዳደር ደረጃ ዕውቅና መስጠት | 7% | 3 | 3 | - | - | - | 3 | | | |
| | | | | በሞተር ሳይክል ህጋዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር በማድረግ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር አወዳድሮ እውቅና መስጠት | 7% | 3 | 3 | - | - | - | 3 | | | |
| | በጀት10% | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | 10% | የተመደበው በጀትና የተሰሩ ስራዎች ንጽጽር | 10% | 100% | 100% | 25% | 25% | 25% | 25% | | | |
| | የውስጥ አሰራር 60% | የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ፤ የደንብ ተላላፊዎችና አደጋ መረጃን ማስተላለፍ | | በ2012ዓ.ም አጠቃላይ አደጋ በ10% መቀነስ በመቶኛ | 5% | 10% | 10% | -- | -- | -- | 10% | | | |
| | | | | በሰው የሚደርሰውን ሞት በ10% መቀነስ በመትኛ | 5% | 10% | 10% | -- | -- | -- | 10% | | | |
| | | | | በንብረት የሚደርሰውንጉዳት በገንዘብ ሲተመን 10% መቀነስ በመቶኛ | 5% | 10% | 10% | -- | -- | -- | 10% | | | |
| | | | | የደንብ ተላላፊዎችሪፖርት ከነሪኮርዱ በየሳምንቱ ማስተላለፍ በቁጥር | 4% | 52 | 52 | 13 | 13 | 13 | 13 | | | |
| | | | | የአደጋ የተተነተነ መረጃ በየሳምንቱ ሪፖርት ማስተላለፍ በቁጥር | 4% | 52 | 52 | 13 | 13 | 13 | 13 | | | |
| | | የቁጥጥር ሥራዎች መስራት | | ደንብ ቁጥር 395/ 2009 ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በመንግድ ላይ ቋጥጥርና ክትትል ማድረግ | 5% | 365 | 365 | 92 | 91 | 91 | 91 | | | |
| | | | | በመንግስታዊ፣ ህዝባዊና ኃይማኖታዊ በዓላት፣ በትምህርትተ ቋማት መክፈቻና መዝጊያ ወቅት፣ እንዲሁም የተዘረጉ አሰራሮች አተገባበር ዙሪያ ድንገተኛ የሆነ የትራንስፖርት ቁጥጥርና ክትትልማድረግ | 4% | 80 | 84 | 21 | 21 | 21 | 21 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | አብይና ቴክኒክ ኮሚቴ ስብሰባዎች | 4% | 12 እና 24 | 12 እና 24 | 3 እና 6 | 3 እና 6 | 3 እና 6 | 3 እና 6 | | | |
| | | የእንጅኔሪንግ ሥራዎች | | ጋሪዎች አንፀባራቂ ምልክት እንዲያደርጉ ማድረግ | 4% | 500 | 500 | 125 | 125 | 125 | 125 | | | |
| | | | | የእግረኛ ማቋረጫ ቦታዎች ላይ ዜብራ ማቋረጫዎች መቀባት | 5% | 120 | 130 | 32 | 32 | 33 | 33 | | | |
| | | | | አለም አቀፍ የመንገድ ዳር ምልክቶችንና ገላጭ ጽሁፎችን ማኖር | 5% | 90 | 100 | | | 50 | 50 | | | |
| | መጣጣሪ ና ዕድገ ት 10% | የግንዛቤ ሥራዎችን ማስጨበጥ | 10% | ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ  የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የህዝብ ንቅናቄ ስራ ተጠናክሮ ስለመሰራቱ | 1% | 230 | 230 | 55 | 55 | 60 | 60 | | | |
| | | | | በአመቱ ወስጥ የተዘጋጀ መድረክ ብዛት በዞን ደረጃ | 1% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | በዞኑ ዉስጥ ባሉ በእያንዳዱ ወረዳዎች በዓመት 6 ጊዜ | 1% | 6 | 6 | 1 | 1 | 2 | 2 | | | |
| | | | | በዞኑ ዉስጥ ባሉ በእያንዳዱ ቀበሌያት በዓመት 12 ጊዜ | 1% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | በት/ቤት አዲስ የመንገድ ደህንነት ክበባት ማደራጀት ማቋቋምና የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ | 1% | 110 | 120 | 30 | 30 | 30 | 30 | | | |
| | | | | ነባር የትቤት ክበባት ማጠናክር የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ | 1% | 345 | 455 | 113 | 113 | 114 | 114 | | | |
| | | | | አዲስ የቀበሌ መንገድ ደህንነት ኮሚትዎችን ማቋቋም የመንገድ አጠቃቀም ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ | 1% | 22 | 44 | 11 | 11 | 11 | 11 | | | |
| | | | | ነባር የቀበሌ መንገድ ደህንነት ኮሚቴዎችን ማጠናከርና የመንገድአጠቃቀም ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ | 1% | 300 | 354 | 88 | 88 | 89 | 89 | | | |
| | | | | በመንግስታዊ ህዝባዊና ሀይማኖታዊ ስብሰባዎች በመገኘት በዞን፣ ወረዳና ከተማ መዋቅሮች ገጽ ለገጽ ማስተማር | 1% | 4,000,000 | 4,000,000 | 1,000,000 | 1,000,000 | 1,000,000 | 1,000,000 | | | |
| | | | | በዞን ወረዳና ከተማ አስተዳዳር  እግረኞችን ተሳፋሪዎችን አሽከርካሪዎችን ተሽከርካሪዎችን የመንገድ አጠቃቀም የሚያስተምር ብሮሸሮችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት | 1% | 3,000 | 3,000 | 750 | 750 | 750 | 750 | | | |
| | | | | በደቡብ ኤፍኤምና እና በአካባቢ ሬዲዮ በዓመት 240 ሰዓታት የመንገድ  ደህንነት ትምህርት ኘሮግራም እንዲተላለፍ ማድረግ | 1% | 52 | 52 | 13 | 13 | 13 | 13 | | | |
| | | | | አሽከርከሪዎች አደጋን ተከላክለው እንዲያሽከረክሩ የሚያግዝ ስልጠና መስጠት | 1% | 6,800 | 6,800 | -- | -- | -- | 6,800 | | 200000 | |

# በትራንስፖርት ዘርፍ የት/አቅ/አደ/ስምርት ቡድን የ2013 ዓ.ም ዓመታዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ

| ተቁ | ዕይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት % | መለኪያዎች | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች- | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብዓመት | | | | ፈጻሚ አካል | በጀ ት | ምር ሚራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | | | |
| 1 | ተገልጋይ ኅ/ሰብ 20% | የዞኑን የመንገድ ትራንስፖርት ሽፋንና ጥራት በበቂ ሁኔታ የማሳደግሥራ በማከናወን የተገልጋዩን ኅ/ሰብ እርካታ 95% ማድረስ | 4% | 6 ወቅቱን ጠብቆ የታደሰ የማህበራት ፈቃድ ዕድሳት በቁጥር | 1% | 6 | 6 | 0 | 6 | 0 | 0 | | | |
| | | | | 2 በነፃ ስምሪት አሠራር ያልተሸፈኑ የስምሪት መስመሮችን በፋራንቻይዝ አግባብ ማስራት በቁጥር | 2% | 2 | 2 | 2 | 0 | 0 | 0 | | | |
| | | | | በዞኑ አሁን ያሉትን የህዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎችን በቁጥር በ100 መጨመር | 1% | 80 | 100 | 25 | 25 | 25 | 25 | | | |
| | | 2. በዞኑ የስምሪት አገልግሎት የሚሠጥባቸውን መናኸሪያዎች ደረጃ ማሻሻልና 2 አዳድስ ለማስገንባት ሙያዊና ድጋፋዊ እገዛ ክትትል ማድረግ | 5% | በዞኑ የሚገኙ መናሓሪያዎች እንድታጠሩ ማድረግና መሰረተ ልማት እንድሟላ ማድረግና /የመናኃሪያ ደረጃ ማሻሻል በቁጥር | 2% | 10 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | በዙር ድጋፍ የተደረገላቸው መለስተኛና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ማህበራትን | 1% | 12 | 12 | 4 | 4 | 4 | 4 | | | |
| | | | | በዞኑ የሚገኙ በ2 ከተሞች በተጠኑ ስምሪት መስመሮች ላይ የተሳፋሪ ዕቃ መጫኛና ማውረጃ ፈርማታዎችን መለየት በቁጥር | 1% | | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | በነጻ ስምርት ዙሪያ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ተገቢን ምላሽ መስጠት | 1% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | 4% | ከዞን እስከ መናኃሪያ ያሉ የትራንስፖርት አፕሮሽናል ስራዎች በቢፒአር ጥናት መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸውን ድጋፋዊ ክትትል ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት በቁጥር | 2% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | በዞኑ መናኃሪያዎች ውስጥ የህ/ማመ/ስም/ማውጫ ፈቃድ አሰጣጥ የስምርት መፍቀጃ ቅጽ አጠቃቀምና የስምርት መረጃ አያያዝ ዙርያ የትራ/ሪፎርም ስራዎች ዙርያ የተጠናከረ ክትትል ማድረግ | 2% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 3% | የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያ በማድረግ በክልል ደረጃ የሚዘጋጀውን ታሪፍ በዞን ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 1% | የታሪፍ ለውጥ ሲኖር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | በዞኑ ላሉ መናሐሪያዎች በመንገዶችና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ስም የመናሐሪያ የባለቤትነት ፕላን ማሰራት | 2% | 8 | 19 | 4 | 4 | 6 | 5 | | | |
| | | | 4% | በደንቦችና መመሪያዎች በተገቢው ሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተል በዙር | 1% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | በዞኑ በሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች የታክስ ማህበራትን ማደራጀት በቁጥር | 1% | 2 | 4 | | 2 | 2 | | | | |
| | | | | በዞኑ በሚገኙ ሪፎርም ከተሞች የታክስ ማህበራትን የኦፕሬተርነት ፈቃድ ማደስ በቁጥር | 1% | 2 | 7 | 2 | 2 | 2 | 1 | | | |
| | | | | የነዳጅ ዋጋ በፌደራል ስክለስ ያንን መነሻ በማድረግ በከተማ አስተዳደሮች የታክስ ታሪፍ ማዘጋጀት | 1% | የታሪፍ ለውጥ ሲኖር | 6 | 3 | 3 | | | | | |
| 2 | በጀት 10% | ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም | 10% | የተሰሩ ሥራዎች ከተመደበው በጀት ንጽጽር በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| 3 | የውስጥ አሠራር ሥራ ሂደት 60% | የትራንስፖርት ስምሪት አፈጻፀም መረጃ በማሰባሰብና በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ማስተላለፍና ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት | 26% | ዕለታዊ የመናኃሪያ የስምርት አፈጻጸም መረጃዎችን በዕለት በሳምንት በወርና በዓመት ማደራጀት በዙር | 3% | 12 | 12 | 3 | 3 | | 3 | | | |
| | | | | ዞናዊ የስራ ሂደቱን ዕቅድና ሪፖርት ማዘጋጀት በዙር | 2% | 4 | 12 | 3 | 3 | | 3 | | | |
| | | | | ከዞን ተነሽ የሆኑ የወርሃዊ ስምርት መርሐ-ግብር ማጽደቅና ክትትል ማድረግ በዙር | 2% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | በዞኑ ውስጥ የመናሐሪያ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡትን በጥቃቅንና አነስተኛ ማደራጀት | 2% | 17 | | | | | | | | |
| | | | | የዕቅዶቻችንን አፈጻጸም ዙሪያ ከወረዳዎችና ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር መወያየት በዙር | 4% | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | ዕለታዊ ሳምንታዊና ወርሃዊ የስራ ሂደቱን ክንውን መገምገምና ወርሃዊ ግብረ መልስ ለማህበራትና ለወረዳዎች መስጠት በዙር | 3% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | ከአጎራባች ዞኖች ጋር በስምርት አፈጻጸምና በታሪፊ አሰራር ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማስወገድ መድረክ ማዘጋጀት | 2% | 2 | 2 | | 1 | | 1 | | | |
| | | | | በዞኑ በሚገኙ መናሐሪያዎች የተሳፋር የመጫንና የማውረድ አገልግሎትን በማህበራት እንድሰጥ ማድረግ | 2% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በይርጋዓለም ፤አለታ ወንዶና ወንዶ ገነት ከተማ የስምርት መስመሮችን ማጥናትና ታሪፊ ማዘጋጀት | 1% | የታሪፍ ለውጥ ሲኖር | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | | በዞኑ ስራ ሂደትና በወረዳዎች የሰው ኃይል ባልተሟላባቸው እንድሟሉ ክትትል ማድረግ | 1% | 2 | 2 | 1 | | 1 | | | | |
| | | | | በበዓላትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋሚት ተማሪዎች በሚለቀቁበት ወይም በሚገቡበት ወቅት በልዩ ጊዜ መመሪያ መሰረት አገልግሎት መስጠት በዙር | 4% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | የዞኑን የመንገድ ትራ/ሽፋንና ጥራት በበቂ ሁኔታ የማሳደግ ስራ በማከናወን የተገልጋዩን ህብረተሰብ ዕርካታ ማሳደግ | 34% | በዞን በወረዳና በከተማ መዋቅርና በዞኑ በሚገኙ መናኃሪያዎች ውስጥ ኪራይ ሰብሳብነትን ለመቅረፍ የምያግዝ በየወሩ ግምገማ ማድረግ | 5% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| | | | | በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ የህ/ማመ/ተሽ/ በመመሪያው መሰረት ደረጃ መስጠት | 7% | 400 | 400 | 400 | | | | | | |
| | | | | በበጀት ዓመቱ ዞናዊ የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ መድረክ ማዘጋጀት | 2% | 1 | 2 | | 1 | | 1 | | | |
| | | | | የዞኑን የመንገድ ትራ/ሽፋንና ጥራት በበቂ ሁኔታ የማሳደግ ስራ በማከናወን የተገልጋዩን ህብረተሰብ ዕርካታ ማሳደግ | 4% | 85% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | | ቀደም ስል በነበሩ መስመሮች ላይ አድስ ተጨማሪ መስመሮች መጨመር | 4% | 20 | 5 | 1 | 1 | 2 | 1 | | | |
| | | | | በዞኑ ውስጥ የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ የሚሰጡ አነ/መለ/የህዝብ ማመላለሻ ማህበራትን ቁጥር ከ6 ወደ 7 ማሳደግ | 4% | 6 | 7 | 1 | | | | | | |
| | | | | የተሳፋሪዎችን ቁጥር ማሳደግ | 5% | 5,078,230 | 5,500,000 | **1,375,000** | **1,375,000** | **1,375,000** | **1,375,000** | | | |
| | | | | በየ15 ቀኑ የቀረበ የለውጥ ቡድን ውይይት ሪፖርት በዙር | 3% | 24 | 24 | 6 | 6 | 6 | 6 | | | |
| 4 | መማማርና ዕድገት 10% | በሥራ ሂደቱ ከዞን እስከ መናኸሪያ ለሚገኙ ፈፃሚዎች ለማነበራት ለቦርድ አመራር አካላት ለዋና ሥራ አስካጆችና ቅርንጫፍ ሥራ አስካጆች የኦፕሬሽንና የአስተዳደር ሠራተኞች በጥቅሉ ታዋናዮች ከመንገድ የህዝብ ትራንስፖርት ጋር በተያያዙ ሥልጠና ርዕሶቸች ላይ ኤች አይ ቪ ኤድስንና | 10% | 440/መለ/የህ/ማመ/ማህበር የተደራጁ የቦርድ አመራር አካላትና ሥራ አስካጆችና ለኦፕሬሽን አስተ/ሰራተኞች ስራ አስኪያጆችን በኦርጋናይዘሽን ማነጅመንትና በትራንስፖርት ፕላንግ ስርዓተ ጾታና ኤች አይቪ የግንዛቤ ስልጠና መስጠት በቁጥር | 5% | 440 | 450 | 112 | 113 | 112 | 113 | | | |
| | | | | የህዝብ የመንገድ ትራ/አገል/ለሚሰጡ ኦፕሬተሮች በትራ/አዋጆች፤ደንቦች፤መመሪያዎችና ማኑዋሎች ላይ ስልጠና መስጠት መመሪያዎች እንድተገበሩ መደገፍ | 3% | 200 | 300 | 75 | 75 | 75 | 75 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሥርዓት ያታን ሜይንስትር ሚንግ ባደረገ መልኩ ማሰልጠን | | በወረዳና ከተማ አስ/አድስ ለተቀጠሩና ለተመደቡ አመራሮችና ባለሙያ በስራ ሂደቱ ህግ ማዕቀፎችና በስራ ሂደቱ አሰራር ላይ ስልጠና መስጠት | 2% | 63 | 63 | | | 63 | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | 150, 000 | |

| የጭነት ትራንስፖርት | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | ዐይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት % | መለኪያዎች | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች- | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | | ፈጻሚ አካል | በጀት | ምር ሙራ |
| | | | | | | | | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | | | |
| 1 | ተገልጋይ 20% | ነባር የጭነት ማመላለሻ ማህበራትን በአዲስ መልክ ደረጃ መስጠት፣ ሥሌዳ ማስለወጥ፣<br>- አዲስ የጭነት ማመላለሻ ማህበራት ማደራጀት፣<br>- ለነባርና አዲስ ማህበራት በድርጅት ወይም በኩባንያ ለሚደራጁ ባለሀብቶች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ<br>- ለተሽከርካሪ ባለንብቶች የማህበር ዝውውር አገልግሎት መስጠት፣ | 20% | ብቃቱ የተረጋገጠ ነባር ጭነት ማህበራትን በማደራጀት የተሰጠ የደረጃ ፍቃድ፣ በተሽከርካሪ ቁጥር | 5% | 340 | 400 | 100 | 100 | 100 | 100 | | | |
| | | | | ግልጽና የጠራ ማህበራት አደረጃጀት በመዘርጋት፣ድጋፍ ማድረግ/ በቁጥር/ | 5% | 12 | 6 | | 2 | 2 | 2 | | | |
| | | | | የሥሌዳ ለውጥ የተደረገላቸውና ደረጃ የተሰጣቸው ተሽከርካሪዎች፣ | 4% | 45 | 147 | 36 | 36 | 36 | 37 | | | |
| | | | | ተደራጅተው ፍቃድ የወሰዱ አዲስ ማህበራት፣ | 2% | 1 | 2 | | 2 | | | | | |
| | | | | ለነባርና ለአዲስ ማህበራት በድርጅት ወይም በኩባንያ ለተደራጁት የተደረገ ክትትልና ድጋፍ፣ | 4% | እንደመጣ | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | | | |
| 2 | በጀት 10% | ለሥራ ሂደት የመመደበው በጀት በተገቢው በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣ | 10% | በሥራ ላይ የዋለ በጀት | 10% | 3 | | | | | | | | |
| 3 | የውስጥ አሠራር 60% | ለተደራጁ ማህበራት፣ ለድርጅቶች፣ ለኩባንያዎች ውጤታማ አገልግሎት አሳጣጥ ማሳደግ፣ | 60% | ውጤታማ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ | 30% | | | | | | | | | |
| | | | | ለጭነት ትራንስፖርት የተከለለ መናኸሪያና የግንባታ አፈጻጸም ማሳደግ፣ | 20% | | 2 | 1 | | 1 | | | | |
| | | | | ያደገ አፈጻጸምና የጨመረ ተነሳሽነት እንዲኖረው የተደረገ፣ | 10% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | መማማርና እድገት 10% | የሰው ኃይል የመፈጸም ብቃትና ተነሳሽነት ማሳደግ፣ | 5% | መፈጸም ብቃትና ተነሳሽነት የደገ የሰው ኃይል፣ | 5% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | በወረዳዎች መናኸሪያ በመከለልና የሥራ ሂደቱንንና የማህበራት አቅም ማሳደግ፣ | 5% | አቅማቸው የተገነባ የወረዳ ጽ/ቤቶችና ማህበራት | 5% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | | | |
| | | | | | | | | | | | | | 115,500 | |

## የልማት ዕ/ኢኮ/አስ/ክ/ግ/ግ ዳይሮክቶሬት የ2013ዓ.ም የውጤት ተኮር ዕቅድ

| ተ ቁ | ዕይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት | መለኪያ | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብዓመት | | | | በጀት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛሩብ | 2ኛሩ ብ | 3ኛሩብ | 4ኛሩብ | |
| 1 | ተገልጋይ 20 % | በዞን መምሪያና በወረዳ በመንገድና ትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በBPR እና BSC መሰረት የተሳለጠ እንድሆን ድጋፍ ማድረግ | 15% | ከ2008-2012 ያለውን የGTP እቅድ አፈጻጸም ሰነድ ማዘጋጀት በዙር | 2% | -- | 1 | | 1 | | | |
| | | | | ከ2008- 2012 ያለውን የGTP እቅድ መከለስ በዙር | 3% | 1 | 1 | | 1 | | | |
| | | | | የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ እቅድ ማዘጋጀት በዙር | 2% | 2 | 2 | 1 | | 1 | | |
| | | | | የURRAP ፕሮጀክት ስራዎችን መከታተል መደገፍና መገምገም በዙር | 4% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | በዞኑ የሚገነቡ የካፒታል ፕሮጀክት ግንባታ ስራን መገምገምና መከታተል በዙር | 4% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | ለወረዳና ለዞን መምሪያ ስራ ሂደቶች በልማትና በመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም ላ1ይ ግብረ-መልስ መስጠት | 5% | የተሰጠ ግብረ-መልስ በዙር | 5% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 2 | በጀት | ለበጀት ዓመቱ የተመደበውን በጀት ከአላስፈላጊ ወጪዎችና | 10% | ለስራ ሂደቶች አመታዊ በጀት በመደልደል በማነጅመንት | 3% | 1 | 1 | 1 | | | | |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 10% | ከብክነት በጸዳ መልኩ ስራ እንድውል ድጋፍ ማድረግ | | እንድጸድቅ ማድረግ በዙር | | | | | | | | |
| | | | | ለካፒታልና ለመደበኛ ፕሮጀክቶች የተመደበው በጀት ለማስተዳደር ክትትል ማድረግ | 4% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | | | | የስራ ሂደቶችን የበጀት አጠቃቀም ሌጀር በማዘጋጀት መመዝገብና ክትትል ማድረግ በዙር | 3% | 12 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 | |

| ተ.ቁ | ዕይታዎች | ግቦች/ዋና ዋና ተግባራት | ክብደት % | መለኪያ | ክብደት % | የአፈጻጸም መነሻ 2012 | ዒላማዎች | የ ሚከናወንበት ጊዜ በሩብዓመት | | | | በጀት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | 1ኛሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ | | |
| 3 | የውስጥ አሰራር 60 % | በወረዳና በዞን የስራ ሂደቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች በBPR እና BSC ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን መከታተል መደገፍና የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት | 12% | የተደረገ ድጋፍና ክትትል በቁጥር | 12% | 12 | 24 | 3 | 3 | 3 | 3 | | |
| | | የለውጥ ስራን በየ15 ቀኑ መገምገምና ለመምሪያ ሪፖርት ማቅረብ | 8% | የለውጥ ስራን በየ15 ቀኑ በመገምገም ለመምሪያ የቀረበ ሪፖርት | 8% | 20 | 24 | 6 | 6 | 6 | 6 | | |
| | | | 8% | ለኮማንድ ፖስት የተሰጠ ግብረ መልስ | 8% | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | | |
| | | የፈጻሚ ሰራተኞች የለውጥ ቡድንና የተቋም ምዘና ከስራ ሂደቶች ጋር ማዘጋጀትና ድጋፍ ማድረግ | 8% | የተደረገ ምዘና በዙር | 8% | 2 | 2 | | 1 | | 1 | | |
| | | የኮማንድ ፖስት ሪፖርትን አደራጅቶ ለመምሪያ ማቅረብና ማስገምገም | 5% | የተዘጋጀና የተሰራጨ ሪፖረት በዙር | 5% | 24 | 24 | 6 | 6 | 6 | 6 | | |
| | | የዜጎች ቻርተር ማዘጋጀት | 4% | የተዘጋጀና የተሰራጨ የዜጎች ቻርተር በቁጥር | 4% | -- | 200 | | 200 | | | | |
| | | ዓመታዊ መጽሔት ማዘጋጀት | 5% | የተዘጋጀና የተሰራጨ መጽሔት በቁጥር | 5% | -- | 100 | | | 100 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | አቅም ግንባታ 10% | ለወረዳ ጽ/ቤት ሓላፊዎችና ባለሙያዎች ስለ ለውጥ ስራዎችና ስለ እቅድ አፈጻጸምና ሪፖርት ግንዛቤ ማስጨበጥ | 4% | ለወረዳ ጽ/ቤት ሓላፊዎችና ባለሙያዎች የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በዙር | 4% | - | 2 | | 1 | | 1 | | |
| | | | 2% | ለመምሪያ ሲቪል ሰርቫንት የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በዙር | 2% | -- | 2 | 1 | | 1 | | | |
| | | | 4% | ከመምሪያ የሚሰጡ ተግባራትን በጊዜና በጥራት ሰርቶ ማቅረብ በመቶኛ | 4% | - | 12 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100,000 | |

**ክትትልና ድጋፍ፣የሪፖርትና ግምገም ሥርዓት**

የልማትና የለውጥ ሰራዊት ግንባታ መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም፣መመሪያዎች፤ደንቦችና የዜጎች ቻርተርን ያገናዘበ የአገልግሎት አሰጣጥን መተግበር፤ለተገልጋዩ የሚሰጡ አገ/ት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ተገልጋዩ የመጣበትንና አገልግሎት ያገኘበትን ሰዓትና የተሰጠውን አገ/ት የሚያሳይ ቅጽ መጠቀም፤ ከአፈፃፀም ሂደቱ በመነሳት የተገኘውን ዉጤትና ፋይዳ ክትትል በማድረግ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በሴክተር ደረጃ በተዘጋጀው የልማትና የለውጥ አመራር ሥራዎች መከታተያ ቼክ ሊስት መሠረት ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡የሴክተሩ ማኔጅሜንት በየወሩ እየተሰበሰበ አፈፃፀሙን ይገመግማል፡፡ሥራዎች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸውን ባለሥልጣኑና እያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት ይከታተላል፡፡እያንዳንዱ የሥራ ክፍል በየሩብ አመት የአፈፃፀም ሪፖርታቸውን ያቀርባሉ፡፡እንደ ሴክተር እንደ ዘርፍና እንደየ ሥራክፍል ባህሪ አንፃር እየተቀናጀ በየወሩ እና በየሩብ ዓመት የመስክ ምልከታ ይደረጋል፡፡በየወቅቱ የተመዘገቡ ውጤቶችና የታዩ ድክመቶችን በመለየት አስፈላጊውን እርምት እርምጃ የማድረግና የአፈፃፀም ሪፖርቱን በየደረጃው የታቀዱ ቁልፍ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት በየሩብ ዓመቱ በሪፖርት የማቅረቢያ ቀን ገደብ መሠረት እየተጠቃለለ ለሚመለከታቸው አካላት የሚተላለፉ ይሆናል፡፡በቀጣዩ የሥራ ጊዜ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የውድድር መንፈስ በሚያዳብር መልክ በየደረጃው በየሩብና በዓመቱ መጨረሻ በሴክተሩ በተዘጋጀው የልማትና የለውጥ ሥራዎችን አጠቃላይ የአፈፃፀም ግምገማ እየተካሄደ ግብረ-መልስም ይሰጣል፡፡የተሻሌ ውጤት ያስመዘገበው ቡድን/ዘርፍ እና በየደረጃው ያሉት ፈፃሚዎች ድረስ ይሸለማሉ ይበረታታሉ፡፡

**ታሳቢ የተደርገው የሚጠበቁ ጉዳዮች**

- በሴክተሩ የ1ለ5፤ለውጥ ቡድን እና ማኔጅሜንት አደረጃጀትእና የለውጥ ሥራዎች ማስፈፀሚያ ዕቅድ መኖር፤
- የመልካም አስተዳደርና ፀረ-ኪራይ ሰብሳብኔት ዕቅድ መኖር
- የህዝብ ክንፍ ዕቅድ መኖር
- የሴክተሩ ትራንስፖርት አገልግሎትና መንገድ ልማት ግንባታ በተቀመጡ አሰራሮች፤መመሪያዎችና የዜጎች ቻርተር መሠረት ተጠናክረው ይቀጥላል
- ሴክተሩ ለ2012 በጀት ዓመት የጠየቀው በጀት ሥራን በሚያሰራ መልኩ ይፈቀዳል
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለን ግንኙነት የተጠናከረ ይሆናል
- 50 ፐርሰንት የአፈር ሥራ በህብረተሰብ ተሳትፎ ለቀበሌ ተደራሽ መንገዶች ይሰራል
- የዝናብና ወቅቶች መፈራረቅ በመደበኛው ሁኔታ ይከናወናል
- በዞንና በወረዳ የሚገኙ የሰክተሩ መዋቅሮች ኃላፍነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ
- የፈፃሚዎች ዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎች በተቀመጡ ጊዜ ይከናወናል

- በየደረጃው ከሚገኙት ሴክተሩ መዋቅሮችና ባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ አፈፃፀም ላይ መግባባት ይፈጠራል

**ልያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ልያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች**

- ሴክተራችን ለበጀት ዓመት የጠየቀው በጀት ለታቀደው ሥራ በቂ ላይሆን ይችላል
- የባለድርሻ አካላት ትብብር ማነስ
- በገበያ ላይ የግብዓት እጥረት አና የዋጋ ንረት
- የማሽኔሪዎች ብልሽት
- በአንዳንድ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ
- ለቀበ/ተደ/መን/ግን/50% በህብረተሰብ ተሳትፎ ተሰርቶ በወቅቱ ዝግጁ ያለመሆን

**የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የሚፈቀደውን ውስን በጀት በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም
- የባለድርሻ አካላትን የተሟላ ትብብር ለማግኘት በህዝብ ክንፍ ዕቅድ መመራት
- በገበያ ላይ ያለውን የማሽኔሪ አቅርቦትና የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በሥራዎች ቅድም ተከተልና ያሉንን ማሽኔሪዎች በአግባቡ በቅድመ ዝግጅት ወቅት ማስጠገንና አቀናጅቶ መጠቀም
- ስራዎችን በየትኛው ሩብ ዓመት መሥራት እንዳለብን የድርጊት መረሀ-ግብር ማዘጋጀት
- የህብረተሰብ ተሳትፎን ለማሳደግ በየደረጃው ከሚገኙ የመስተዳድር ምክር ቤት፤ቋሚ ኮሚቴዎችና አደረጃጀቶች ጋር በቅንጂት መሥራት